# ኢትዮጵያ ውስጥ በሰብዓዊ  አካባቢዎች የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታ ምክር ቤት (ዩኤንኤስሲአር) ውሳኔ 1325 አተገባበር ግምገማ ማጠቃለያ

## በኢትዮጵያ ውስጥ የስነ ጾታ፣ ሰላምና ጸጥታ ተፈላጊነት

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ክልል ውስጥ በሰላም ድርድር እና በእርቅ ተግባራት ወሳኝ ሚና እየተጫወተች ትገኛለች፤ ከእነዚህ መካከል አንዱ ጉልህ ማሳያ በቅርቡ የደቡብ ሱዳንን የሰላም ድርድር እየመራች መሆኗ ነው፡፡በዚህ ረገድ፣ የአፍሪካ ቀንድ ሴቶች በሰላም ድርድሮች እንዲሳተፉ በደግነት በሮቿን ከፍታ ተቀብላችዋለች፡፡ ቤጂንግ ዲክላሬሽን ኤንድ ፕላትፎርም ፎር አክሽን እ.ኤ.አ. 2014 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሪፖርት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሒውማኒተሪያን ቀውስ ከስነ ጾታ አንጻር ለመፍታት መሞከር ያለውን አስፈላጊነት ይመክራል (የሴህወጉሚ)፡፡ በአሁን ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ በአሶሳ፣ ዶሎ አዶ፣ ጋምቤላ፣ ጅጅጋ፣ ሰመራ እና ሽሬ አካባቢ በ23 ካምፖች ከሚኖሩት ወደ 630,000 ገደማ የሚጠጉ ስደተኞች መካከል አብዛኞቹ ሴቶችና ህጻናት ናቸው (ዩኤንኤችሲአር 2015)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ወደ 414,000 የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሲሆን ከእነኚህም መካከል 46 በመቶ ያህሉ ሴቶች ናቸው (አይዲኤምሲ ሪፖርት እ.ኤ.አ. 2015)፡፡ ኢትዮጵያ ለአይዲፒ እና ለስደተኞች ከሰጠችው ምላሽ ባሻገር ኢትዮጵያ በሰላምና ደህንነት አጀንዳ ላይ የስነ ጾታን ጉዳይ ከምታጣምርበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ክርክር ኢትዮጵያ ሴት የሰላም አስከባሪ አባላትን በመላክ በአለም ተቀዳሚ በአፍሪካም በአጠቃላይ አራተኛ መሆኗ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያ ፖሊስ እና የጦር ሰራዊት ውስጥ የሴቶች ቁጥር እየጨመረ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የስነ ጾታ እና ሴቶችን የማብቃት አጀንዳ ከህገ መንግስቱ የሚመነጭ ሲሆን ስነ ጾታም እንደ ብሔራዊ ደህንነት ፖሊሲ በመሳሰሉ አያሌ ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎች ውስጥ ይሰራጫል፡፡ በሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮች ላይ የኢትዮጵያ ፖሊሲና ህግጋት ምልከታ የሴቶች ጉዳይና በሰብዓዊነት ቅኝት የማህበራዊና እና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶቻቸው እውቅና አንደተሰጠው ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ እንደ ኢጋድ መስራች አባል ሀገር የተባበሩት መንግስታት ጸጥታ ምክር ቤት 1325 እና 1820 ድንጋጌ የ2013 የኢጋድ ሪጅናል የድርጊት እቅድን አጽድቃለች፡፡

## የግምገማው ዋና ዋና ግኝቶች

- ኢትዮጵያ የዩኤንኤስሲአር 1325 (የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታ ጥበቃ ም/ቤት ውሳኔ 1325) ይዘቶችን ስትተገብር ቆይታለች፣ አሁንም እየተገበረች ትገኛች፡፡ ነገር ግን የግድ በልዩ የዩኤንኤስሲአር 1325 ብሔራዊ የድርጊት መርሃ-ግብር ውስጥ አላካተተችውም፣
- ዩኤንኤስሲአር 1325 አራቱ ምሰሶዎች ባሉበት ሁኔታ ከኢትዮጵያ የሕግ እና የፖሊሲ ድንጋጌዎች ጋር የሚቀናጁ ናቸው፣
- የሴቶች ጉዳይ በሁሉም ደረጃዎች ላይ በሚገኙት የአገሪቱ የሰላም ባህል እና የሰላም ሂደት፣ እንዲሁም በሁሉም ደረጃዎች ለሚገኙት የግጭት ቅደሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ ስርዓቶች ውስጥ  እንደ ዋነኛ ርእስ  ተካቷል፣
- በክልል እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ ባላት የሰላም ማስከበር ሚና ውስጥ ጾታዊ ጉዳይ እንዲካተት ለማድረግም ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፣
- ኢትዮጵያ እስካአሁን ድረስ በአጠቃላይ በሰላም ግንባታ፣ በተለይ ደግሞ በሴቶች፣ በሰላም እና በፀጥታ አጃንዳዎች  ላይ በሚሰራ ማዕቀፍ ረገድ ተለይቶ የተቀመጠ ፖሊሲ ያላትም፣
- ዩኤንኤስሲአር 1325ን በሚመለከት በባለድርሻ አካላት ዘንድ የእውቀት ውስኑንት፣
- ኢትዮጵያ ውስጥ ለጾታ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት መስጠት እና ሴቶችን የማብቃት አጀንዳ ከአገሪቱ ሕገ-መንግስት የሚመነጭ ሲሆን፣ የጾታ ጉዳይ በሌሎች ብዙ ፖሊሲዎች እና የሕግ ማዕቀፎች ውስጥ ተካቷል፣ እንደ ብሔራዊ የደህንነት ፖሊሲ በመሳሰሉት ውስጥ፣
- ከሰላም እና ጸጥታ ጋር ተያያዥ የሆኑ የኢትዮጵያ ነባር ፖሊሲዎች እና ሕጎች በሰብዓዊ አካባቢ ለሴቶች ችግሮች እና ለማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶቻቸው ጉልህ እውቅና መሰጡትን ያረጋግጣሉ፣
- ኢትዮጵያ ውስጥ በሰብዓዊ አካባቢ ከጾታ እኩልነት ጋር በተያያዘ ዋነኛ የመፍትሔ ትኩረት የተሰጣቸው ወሲባዊ እና ከጾታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶች (ኤስጂቢቪ) ሲሆኑ፣ ሎሎች ጾታዊ ገጽታዎች ግን እኩል ትኩረት አልተሰጣቸውም፣
- በኤስጂቢቪ ላይ የተደረገው ትኩረት በአብዛኛው በኢንተር-ኤጀንሲ ቋሚ ኮሚቴ (አይኤኤስሲ) የኤስጂቢቪ ውህደት ደንብ አማካኝነት የተገኘ ሲሆን፣ ሌሎች የጾታዊ እኩልነት ገጽታዎች ግን አልተገኙም ወይም በባለድርሻ አካላት አይታወቁም፣
- በድርጅታዊ ደረጃ፣ ፈጻሚ አጋሮች (አይፒኤስ) ድርጅታዊ የጾታ ጉዳይ ፖሊሲዎቻቸው እና የጾታ ጉዳይን እንደ አንድ ዋነኛ ክፍል ያካተቱት ደንቦቻቸው ከስደተኞች ጋር ተያያዥ የሆኑ የመፍትሔ እርምጃዎችን ጨምሮ በሰብዓዊ ተግባሮቻቸው ውስጥ ትኩረት እንደሚደረግባቸው ሪፖርቱ ያደረጉ ቢሆንም፣ ከፈጻሚ አጋሮቹ መካከል አንዳቸውም ዩኤንኤስሲአር 1325ን ዋና ዋና ነጥቦች ተቀብለው ከስደተኞች ጋር ተዛማጅ በሆኑት ተግባሮቻቸው ውስጥ አላካተቱም፡፡

ዩኤንኤስሲአር1325 በ4 ዋና ዋና ምሰሶዎች ላይ የተዋቀረ ሲሆን፣ እነርሱም፡- መከላከል፣ ጥበቃ፣ ተሳትፎ እንዲሁም ከሴቶች፣ ሰላምና ደህንነት ጋር በተያያዘ ዋና ዘርፎችን የሚያካትት የሰላም ግንባታና ማገገም ናቸው፡፡ ዳሰሳው እነኚህን ምሰሶዎች እና በኢትዮጵያ የሰብዓዊ ስራ አግባብ ያላቸውን ትግበራ በመገምገም የሚከተሉትን ለማወቅ ችሏል፡፡

**መከላከል፡-** የምሰሶው ትንተና ግጭትና ጾታዊ የወሲብ ጥቃትን ለመከላከል የሚያስችሉ መደበኛና ኢ-መደበኛ እንዲሁም ባህላዊ መንገዶች መቀመጣቸውን ያሳያል፡፡ የሰብዓዊ መብት አካሔድን በመጠቀም የውስጥ ተፈናቃይ ሰዎች (አይፒዎች) ለሴቶች መብት የሚያስፈልገውን ልዩ እውቅና የሚረዱ ሲሆን የዩኤን-ኤስሲአር1325 ዋና ይዘቶችን ግን አላካተቱም፡፡ በተጨማሪም በስራ ላይ የሚገኙ ሲስተሞች በአብዛኛው አጠቃላይ የጾታ ሃይል ሚዛን መዛባትንና የእኩልነት መጓደልን አያትቱም፡፡ ስለዚህም የጾታ/ወሲባዊ ጥቃትንና የጾታ እኩልነት መዛባትን ስረ መነሻዎች አይመለከቱምና የመከላከያ መንገዶችን አያመላክቱም፡፡

**ጥበቃ:** የሴቶችና ልጃገረዶችን አካላዊ ደህንነት መጠበቅ እንዲሁን ከወሲባዊ ጥቃትና ከሌላ አይነት ጥቃቶች እንዲጠበቁ ማድረግ በጠቅላላው በሰብዓዊነት ይዘት ውስጥ የተካተተ ሲሆን በስደተኞች ጉዳይ ውስጥም በልዩ ሁኔታ ተካትቷል፡፡ በውጤቱም ብሔራዊ የህግ ድንጋጌዎች በፖሊሲና በትግበራ ደረጃ የተቀመጡ ሲሆን በሁሉም ደረጃዎች በሚገኙ የማስተባበሪያ ኮሚቴዎችም ይጠናከራሉ፡፡ ቢሆንም ግን የሴቶችና የልጃገረዶች የደህንነት ስጋት በተለይም የዘረፋ ስጋት አልተቀረፈም፡፡ የሴቶች አካላዊ ደህንነት ከፍተኛ እውቅና የተሰጠው ቢሆንም ሌሎች ስጋቶች ግን በበቂ ሁኔታ ትኩረት አልተደረገባቸውም፡፡ ለምሳሌ የኢኮኖሚ ደህንነት ይጠቀሳል፡፡ ሴቶች በካምፕ ውስጥ ስራ ለመስራት ቅድሚያ የሚሰጣቸውም ቢሆንም በብዛት የቅጥር እድል ስለማይሰጣቸው በኢትዮጵያ የካምፕ ፖሊሲ ተጨማሪ ተጽእኖ በሚያመጣው የትምህርት ማነስና የባህል ክልከላ ሳቢያ የኢኮኖሚ ደህንነት ስጋት ይጋረጥባቸዋል፡፡ የህግ ከለላም እንደ አንድ የትኩረት አቅጣጫ የተነሳ ሲሆን ጉዳይ ለመፍታት የሚወስደው ጊዜ ሊያጥር ይገባል፡፡

**ተሳትፎ:** ግኝቶች እንደሚያሳዩት የሴቶች ተሳትፎ በኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲና የፕሮግራም አፈጻጸም ሒደት ውስጥ ታላቅ ተቀባይነት እያገኘ ነው፡፡ ሴቶችን ለማሳተፍ ያለው መስፈርት እና ጥረቶች እንደተጠበቁ ሆነው ስደተኛ ሴቶች በሁሉም ደረጃ በሚገኙ የአስተዳደር መዋቅሮች ሊሳተፉ/ሊታቀፉ ይገባቸዋል፡፡ ይህም ሴቶች በስደተኞች ማዕከላዊያን ኮሚቴዎች በአብዛኛው የማይሳተፉበትን ሁኔታ ያካትታል፡፡ እነኚህ ኮሚቴዎች ዘወትር በእቅድ፣ በአፈጻጸም እና በቁጥጥርና ግምገማ ሒደቶች ላይ ዋና የውሳኔ ሰጪነት ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው ሴቶች ካልተወከሉባቸው የሴቶች ፍላጎትና ድምጽ የሚሰማበት እድል ጠባብ ይሆናል፡፡ አይፒዎች መስፈርት እንደማያደርጉትና በስደተኛ ካምፖች ውስጥ የ50 በመቶ የሴቶች ተሳትፎን እንዳልደነገጉ ለመመልከት ተችሏል፡፡

**እርዳታና ማገገም:** ከእርዳታና ማገገም ጋር የተያያዙ ስራዎች በጾታዊ አትኩሮት እና ሴቶችና ልጃገረዶችን ከወንዶች በተለየ አግናን በመመልከት ላይ ያለሙ መሆናቸውን ግኝቶች ያሳያሉ፡፡ ቢሆንም ግን ሁሉም የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች በበቂነት፣ በኢ-መደበኛነት እና ጊዜን የጠበቁ ከመሆናቸው አንጻር አሁንም ለትችት የሚበቁናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእርዳታና ማገገም አገልግሎቶች የሴቶችና ልጃገረዶችን ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ብቃት የሚያጎለብቱ ሚናዎች ያንሷቸዋል፡፡ አሁን ያሉት የኢኮኖሚ ብቃት ኢኒሼቲቮች በይዘታቸው የሴቶችን ደረጃ ያገናዘቡ አይደሉም፡፡

## አስተያየቶች

### ፖሊሲ

- ዩኤንኤስሲአር 1325 በነባር ብሔራዊ ፖሊሲዎች እና ሰነዶች በማካተት በነባር የሕግ ማዕቀፎች ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፣
- በዩኤንኤስሲአር 1325 ላይ ከቁልፍ ባለድርሻዎችና በሁሉም ደረጃ ከሚገኙ ፈጻሚዎች ጋር መረጃ ለመለዋወጥ የፖሊሲ ውይይት ማድረግ፣
- ዩኤንኤስሲአር 1325 ከፕሮግራም ዕቅድ፣ አፈጻጸምና ቁጥጥር ጋር ለማዋሀድ ለአይፒዎች ደንቦች ማዘጋጀት፣
- በዩኤንኤስሲአር 1325 ሁሉም ምሰሶዎች ተያያዥ የሴቶች ተሳትፎን የሚያሳዩ ተናጥል የጾታ መረጃዎችን መሰብሰብ፣
- በሰብዓዊ አካባቢዎች አስተዳዳሪዊ ማዋቅሮች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ኮታን መወሰን፣

### ፕሮግራም

- በጾታ ሜይንስትሪሚንግ እና በዩኤንኤስሲአር 1325 ላይ ለተለያዩ ባለድርሻዎች ስልጠና መስጠት፣
- በጾታ እኩልነት እና እና ሴቶችን በማብቃት ላይ የግንዛቤ ማጎልበቻ ፕሮግራሞች ማዘጋጀት፣
- በሰብዓዊ ምላሾች ውስጥ በተለይ ለጾታ እኩልነት ፕሮግራም ቀረጻ ላይ የሚውል ሀብት መመደብ፣ ላይ ለጾታ እኩልነት ብቁ የሀብት አመዳደብ ማድረግ፣
- ለኢትዮጵያ የሰላም አስከባሪ ኃይል የስነ ጾታ ስልጠናዎች መስጠት፣
- በካምፖች አካባቢ የሚሰሩ ተጨማሪ ሴት ሰራተኞችን መቅጠር፣
- የሴቶችን ተሳትፎ የሚያበረታቱ ጾታ ተኮር ኮሚቴ እና የማህበረሰብ መዋቅሮችን ማቋቋም፣
- የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ማብቃትን ለማከናወን እንዲቻል፣ ፈጠራ አዳዲስ እና ፈጠራ የታከለባቸው የሴቶች ኢኮኖሚ ማብቂያ ፕሮግራሞችን በሰብዓዊ አካባቢዎች ማዘጋጀት፣
- ለወጣቶች የትምህርትና ክህሎት ግንባታ ፕሮግራሞችን ማሳደግ፣
- በሰብዓዊ አካባቢዎች ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች የሕይወት ክህሎቶች ስልጠናዎች (በአመራር እና በውሳኔ ሰጪነት ላይ) መስጠት፡፡

**ዳራ**

ዩኤን ውሜን ከኦስትሪያ ልማት ኤጀንሲ(ኤዲኤ) እ.ኤ.አ. መስከረም 2015 ባገኘው ቸር ድጋፍ በመታገዝ ኢትዮጵያ ውስጥ በሰብዓዊ አካባቢዎች፣ በተለይም በሽሬ እና በጋምቤላ ውስጥ በሚገኙ የስደተኞች ካምፖች ላይ በማነጣጠር ዩኤንኤስሲአር 1325ን አተገባበር ገምግሟል፡፡ ግምገማው የተመራው በዩኤን ውሜን (የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በፆታ እኩልነት እና ሴቶችን በማብቃት ላይ የሚሰራው አካል) ሲሆን፣ ስራውም የተከናወነው ከኦስትሪያ ልማት ኤጀንሲ (ኤዲኤ) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለግምገማው ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበራቸው ቴክኒካዊ ግብአቶች እና አስተዋፅኦዎች የተገኙት ኢትዮጵያ ውስጥ ከፆታ እኩልነት ለጋሽ ቡድን አባላት፣ በተለይም ከስዊዲን ኤምባሲ፣ ከዩኤንኤፍፒኤ እና ከጣልያን ልማት ተራድኦ ድርጅት ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በሚከተለው አድራሻ ይገናኙ፡ Ethiopia.unwomen@unwomen.org